Seattle Department of Education & Early Learning

# የሲያትል ከተማ የጣፋጭ መጠጦች ግብር (SBT)
# ከቅድመ ወሊድ እስከ ሦስት ዓመት (PN-3) የማኅበረሰብ የገንዘብ ድጋፍ ፕሮግራም
# **የመወዳደሪያ ሀሳብ መጠየቂያው (RFP)** ማጠቃለያ ደጋፊ ሰነድ

***መግቢያ***

የመደበኛ እና የቅድመ መደበኛ ትምህርት መምሪያ (DEEL) ከቅድመ ወሊድ እስከ ሦስት ዓመት ባለው ጊዜ ውስጥ ለግለሰቦች የጤና እና የትምህርት ውጤቶችን ለማሻሻል አገልግሎት ለመስጠት ፍላጎት ያላቸውን ማኅበረሰብን መሠረት ላደረጉ ድርጅቶች (CBOs) የመወዳደሪያ ሀሳባቸውን እንዲያቀርቡ እየጠየቀ ነው።

**ለ2025-2027** ለዚህ መዋዕለ ንዋይ በግምት **$1.49** ሚሊዮን ዶላር ተደራሽ እንዲሆን ይደረጋል። ብቁ የሆኑ ተቋሞች በሁለት ዓመት ውስጥ በድምሩ እክስ **$298,000.00** ዶላር የሚሆን በእያንዳንዱ ዓመት **$149,000.00** ዶላር የሚጠይቅ አንድ የመወዳደሪያ ሀሳብ ማቅረብ ይችላሉ። የገንዘብ ድጋፉ በሲያትል ከተማ የመደበኛ እና የቅድመ መደበኛ ትምህርት መምሪያ (DEEL) በሚተዳደረው በዚህ የመወዳደሪያ ሀሳብ መጠየቂያ ሂደት (RFP) በኩል የሚሰጥ ይሆናል። ይህ የPN-3 የማኅበረሰብ የገንዘብ ድጋፍ የመወዳደሪያ ሀሳብ መጠየቂያው (RFP) ***ሦስት*** ትኩረት የሚሰጣቸው ጉዳዮች አሉት፡-

1. ጤናማ እና ፍትሃዊ እኩልነት ያላቸው ውልደቶች
2. የወላጅ የአእምሮ እና የስሜት ጤና
3. ጥሩ እንክብካቤ እና ትኩረት ሰጪነት መገለጫው የሆነ የእንክብካቤ አገልግሎት

DEEL የተለየ ፍላጎት የሚሰጣቸውን ከነጭ የማኅበረሰብ ክፍሉ ውጭ የሆኑ ማኅበረሰቦች፣ አዲስ ሰፋሪዎች፣ ስደተኞች፣ ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ሰዎች እና የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች ተብለው ለአብነት ያህል የተገለጹ ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ሕዝቦች ለመድረስ፣ በሲያትል ከተማ ውስጥ ለመውለድ የሚጠባበቁ ወላጆችን፣ ተንከባካቢዎችን እና/ወይም አሳዳጊዎችን ለማገልገል ተልዕኮ ያላቸውን ማህበረሰብን መሠረት ላደረጉ ድርጅቶች (CBOs) የገንዘብ ድጋፍ መስጠትን ቅድሚያ በመስጠት ላይ ይገኛል። የተሳካላቸው መወዳደሪያ ሀሳቦች የሁለት ዓመት የገንዘብ ድጋፍ ያገኛሉ።

**ብቁነት** እና የገንዘብ ድጋፍ

በዚህ RFP በኩል የገንዘብ ድጋፍ ለማግኘት ብቁ ለመሆን የመወዳደሪያ ሀሳብ አቅራቢዎች ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ መሆን አለባቸው፡-

- ለትርፍ ያልተቋቋመ ድርጅት (ወይም በአንድ ድርጅት ስፖንሰርነት የተደገፈ) (ማኅበረሰብን መሠረት ያደረጉ ወይም እምነትን መሠረት ያደረጉ ድርጅቶችን ጨምሮ) የ 501(c) ደረጃ ያለው
- ለትርፍ ያልተቋቋሙ የማኅበረሰብ ድርጅቶች ወይም ኅብረቶች ለአብነት ያህል የማኅበረሰብ ተራድኦዎች፣ ጥምረቶች እና/ወይም ሌሎች የሽርክና ቡድኖች የመምሪያውን አስፈላጊ የውል ስምምነት መስፈርቶች የሚያሟላ የፊሲካል ስፖንሰር ለይተው ማሳወቅ ይኖርባቸዋል
- ጎሳዎች እና የጎሳ ድርጅቶች

በተጨማሪም መወዳደሪያ ሀሳቦቹ በሲያትል ከተማ ክልል ውስጥ ለሚኖሩ ተሳታፊዎች አገልግሎት መስጠት አለባቸው።

***ይህ የገንዘብ ድጋፍ አስቀድሞ በሌሎች የህዝብ ዶላር ለሚደገፉ አገልግሎቶች ጥቅም ላይ እንዲውል የታሰበ አይደለም።***

ይህን የገንዘብ ድጋፍ ለማግኘት ብቁ ያልሆኑ ፕሮጀክቶች የሚከተሉትን የመወዳደሪያ ሀሳቦች ያካትታሉ፡-

- ፈቃድ ለተሰጠው የልጅ እንክብካቤ ሥራ ጥራት ያለው ድጋፎችን ወይም ድጎማዎችን ማቅረብ
- የአንድ ድርጅት አጠቃላይ ተግባራትን በመደገፍ ላይ ብቻ ማተኮር
- ከቅድመ-ወሊድ እስከ ሦስት ዓመት ዕድሜ ላይ ያለ ማዕከላዊ ትኩረት ያላደረገ
- ፖለቲካ ነክ የማግባባት ሥራ ላይ ያተኮረ
- በአሁኑ ጊዜ ከ2023-2025 የገንዘብ ድጋፍ የተሰጣቸው PN3 የማኅበረሰብ የገንዘብ ድጋፍ አጋሮች

**የእንቅስቃሴዎች** መርሃ ግብር

| ክስተት | ቀን/ሰዓት |
|---|---|

Seattle Department of Education & Early Learning

| | |
|---|---|
| **የመወዳደሪያ ሀሳብ መጠየቂያው (RFP) የሚከፈተው** | **አገስት 11 ቀን 2025 ዓ.ም** |
| **የRFP መረጃ ክፍለ ጊዜ (ቀድሞ-የተቀዳ)** | **አገስት 11 ቀን 2025 ዓ.ም** |
| **አንድ-ለ-አንድ ለቴክኒካዊ ድጋፍ የተወሰነ ጊዜ** | **ከአገስት 11 ቀን 2025 ዓ.ም እስከ ሴፕቴምበር 2 ቀን 2025 ዓ.ም፣ በቀጠሮ** |
| **የጥያቄ እና መልስ ክፍለ ጊዜ** | **ከአገስት 11 ቀን 2025 ዓ.ም እስከ ሴፕቴምበር 2 ቀን 2025 ዓ.ም** |
| **መወዳደሪያ ሀሳቦቹ መግባት ያለባቸው ቀን** | **ሴፕቴምበር 8 ቀን 2025 ዓ.ም፣ 11:59 ፒ.ኤም** |
| **ማመልከቻ የመገምገም፣ ውጤት የመስጠት እና ውሳኔ የማስተላለፍ ሥራዎች** | **ከሴፕቴምበር 09 ቀን 2025 ዓ.ም እስከ ሴፕቴምበር 30 ቀን 2025 ዓ.ም** |
| **ለአመልካቾች ማሳወቂያ ይላካል** | **ኦክቶበር ወር 2025 ዓ.ም*** |

***ዕለተ ቀኖቹ እና ጊዜያቶቹ ሊለወጡ ይችላሉ***

**ለመወዳደሪያ ሀሳቦች የሚቀርብ ማኅበረሰብን መሠረት ያደረገ ቴክኒካል ድጋፍ**

አቅራቢዎች መወዳደሪያ ሀሳቦቻቸውን እንዲያዳብሩ ልምድ ካላቸው ማኅበረሰብን መሠረት ያደረጉ አማካሪዎች ነጻ ቀጥተኛ ቴክኒካል ድጋፍ (TA) ያቀርባሉ። ይህን የቴክኒክ ድጋፍ መወዳደሪያ ሀሳብዎን ለማዋቀር፣ ከዚህ **የመወዳደሪያ ሀሳብ መጠየቂያ (RFP)** ዋና ዋና ነጥቦች ጋር እንዲስማማ ለማድረግ እንዲሁም የRFP ቴክኒካል መመሪያን ለመገምገም የሚያስችል ድጋፍ ለማግኘት እንዲጠቀሙት እጅግ አጥብቀን እናበረታታለን። የቴክኒክ ድጋፍ ለማግኘት እባክዎ ከዚህ በታች የተጠቀሰውን አማካሪ አግኝተው ለማነጋገር ነጻነት ይሰማዎ።

| ቴክኒካዊ ድጋፍ (TA) አቅራቢ | ዳራ እና ግንኙነት |
|---|---|
| ሀሰን ዋርዴር (Hassan Wardere) | ሀሰን ዋርዴሬ በፕሮጀክት አስተዳደር፣ በትክክለኛ የማኅበረሰብ ተሳትፎ፣ በአቅም ግንባታ፣ በለውጥ አስተዳደር፣ በስልታዊ እቅድ ማውጣት እና አጋርነት፣ በቴክኒካዊ ድጋፍ፣ ወዘተ ልዩ ችሎታ አለው። ሀሰን የሚያቀርበው ድጋፍ የሰዎችን ባህላዊ እሴት እና ማንነት በሚያከብር መልኩ የተነደፈ ስልት በመሆኑ፣ ስልታዊ ሀሳቦችን ለማዳበር እንዲሁም ስኬታማ፣ የፈጠራ ክህሎት የተንጸባረቀባቸው፣ ለችግሮች መፍትሄ የሚያበጁ እና ፍትሃዊ እኩልነት ላይ የተመሠረቱ ፕሮግራሞችን እና አገልግሎቶችን ለመቅረጽ በጥቅም ላይ የሚውል እገዛ እንዲያቀርብ ያግዘዋል። እንዲሁም አዲስ ሰፋሪዎችን እና የስደተኛ ቤተሰቦችን ከሚያገለግሉ ማኅበረሰብን መሠረት ካደረጉ ድርጅቶች (CBOs) ጋር በመስራት ደግሞ ሰፊ ልምድ አለው።<br>መገኛ አድራሻ፡- hassan@bulleconsulting.com |

**የቋንቋ ድጋፎች**

ተጨማሪ የቋንቋ ድጋፍ ከፈለጉ የመደበኛ እና የቅድመ መደበኛ ትምህርት መምሪያ (DEEL) እርዳታ ማቅረብ ይችላል። እባክዎ **DEEL የገንዘብ ድጋፍን** በ**deelfunding@seattle.gov** አግኝተው ያነጋግሩ።

**ተጨማሪ መረጃ**

የገንዘብ ድጋፉ ሙሉ ዝርዝሮች ከቅድመ ወሊድ እስከ ሦስት ዓመት የማኅበረሰብ የገንዘብ ድጋፍ ፕሮግራም የመወዳደሪያ ሀሳብ መጠየቂያው ውስጥ ተቀምጠው ይገኛሉ። ለዚህ የገንዘብ ድጋፍ ፕሮግራም ሁሉም መረጃ እና የማመልከቻ ሰነዶች በDEEL የገንዘብ ድጋፍ ማግኛ መልካም አጋጣሚዎች ድረ-ገጽ ላይ ይገኛሉ፡- http://www.seattle.gov/education/for-providers/funding-opportunities